# የመኢአድ ፕሬዚዳንት አሳፋሪ ንግግር

**ቢላል** 05/16/13

አንድን ግለሰብም ሆነ የፖለቲካ ፓርቲ ለመተቸት ስንነሳ የሚተቸው አካል መልካም ገፅታ ወይም በጐ ጎኑንም መዘንጋት እንደሌለብን አምናለሁ፡፡ ምክንያቱ ደግሞ የሰው ልጅ ሙሉ በሙሉ ከስህተት ሊፀዳ እንደማይችል ሁሉ የሚያስወቅስ ጥፋት ሰርቶ ሲገኝም እንዲሁ ጨርሶ ለቁም ነገር የማይበቃ ከንቱ ፍጥረት ተደርጎ ሊቆጠር አይገባም ከሚል መሰረተ ሃሳብ የመነጨ ቅንነት ነው ማለት ይቻላል፡፡

ከዚህ እምነቴ የተነሳም የሀገራችን ተቃዋሚዎች በኢህአዴግ ላይ ጭፍን ውግዘታቸውን ሲያወርዱበት ለነገ የማይሉ የመሆናቸውን ያህል፣ አንድም ቀን እንኳን መልካም ተግባሩን ትንፍሽ ሲሉ አለመደመጣቸው እጅግ በጣም አምርሬ እንድታዘባቸው አድርጐኛል፡፡ ይሄው እኔ ራሴ የተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲ መሪዎችን ለመተቸት ፈልጌ ብዕርና ወረቀት ሳገናኝም ታዲያ ሚዛናዊ የመሆን ጥያቄ ህሊናዬን ይሞግተው ጀመር፡፡

የዚህ ፅሑፍ ዋነኛ ትኩረት የመኢአድ ፕሬዚዳንት ኢንጂነር ሃይሉ ሻውል ባለፈው ሚያዝያ 25 ቀን 2005 ዓ.ም .ታትሞ ከወጣው አዲስ አድማስ ጋዜጣ ጋር ያደረጉት ቃለ ምልልስ መሆኑ ደግሞ ሚዛናዊ ትችት የመሰንዘር ፍላጎቴን ፈታኝ ሳያደርገው እንዳልቀረ ነው የሚሰማኝ፡፡ እንደ እኔ እምነት ምንም እንኳን አብዛኞቹ የተቃዋሚ ፓርቲመሪዎች በአንድ ሳንባ የሚተነፍሱ እስኪያስመስልባቸው ድረስ፣ ለዚች አገር ችግሮች መፈጠር ብቸኛው ተጠያቂ  ኢህአዴግ ነው በሚል ፍረጃ የሚታወቁ መሆናቸው ባያከራክርም፣ ይህን ጭፍን ውግዘት እጅግ አምርሮ እና አክርሮ በማቅረብ ረገድ አቶ ኃይሉ ሻውል ‹‹ሪከርድ› የሰባበሩየማካበድ ‹‹ሻምፒዮና›› ስለመሆናቸው ግን ከላይ በተጠቀሰው ቀን ለአዲስአ ድማስ ጋዜጣ የሰጡትን ቃለ መጠይቅ ማየት ይበቃል፡፡

በሀገራችን አሁን ያለው የፖለቲካ እንቅስቃሴ ምን እንደሚመስል ሲጠየቁ ‹‹የፖለቲካ እንቅስቃሴ አለ እንዴ ?››በሚል መገረም ጋዜጠኛዋ ላይ እንዳልተሳለቁባት እዚያው በዚያው ደግሞ ‹‹ይህን ሁሉ የፖለቲካ ፓርቲ የሚያራባው ማን ይመስልሻል ?ዘጠና እና ዘጠና አምሰት ተቃዋሚ ፓርቲ አለኮ ነው የሚባለው፡፡ ለምሳሌ ሁለት ተቃዋሚ ፓርቲ ሲመሰረት ሌላ አራት ይፈጠራል፡፡ ማነው የሚፈጥራቸው ካልሽ ራሱ ወያኔ ነው፡፡ ደሞዝ

እየከፈለ የሚያኖራቸው ፓርቲዎች አሉ አይደለ እንዴ?›› ይሉና በተለመደው የበሬ ወለደ ውንጀላቸው እውነታውን ለማምታታት ይሞክራሉ፡፡

ኢህአዴግ የትኞቹን የተቃዋሚ ፓርቲዎች እንዳፈረሰና የትኞቹን በምትካቸው እንደፈጠረ የታመነ ምንጭ ጠቅሰው (በማስረጃ አስደግፈው) ይገልጹላት ዘንድ የአዲስ አድማስ ጋዜጠኛ ከመጠየቅ ባትቦዝንም ክቡር የመኢአድ ፕሬዚዳንት ግን ‹‹ አልጠቅስም…! እሱን አንቺ ራስሽ ጠይቂያቸው ‹‹ኢንቬስትጌሽን ሪፖርቲግ የሚባል አለ አይደለም እንዴ?›› ከማለት ውጭ አንድም ማስረጃ ማቅረብ አልቻሉም፡፡

በ2002ቱ አገር አቀፋዊ ምርጫ ዋዜማ የተዘጋጀውን የምርጫ ስነምግባር ኮድ ከኢህአዴግ ጋር ከተፈራረሙ በሁዋላ መኢአድ ከሒደቱ ስለወጣበት ምክንያት ለጠየቀቻቸው የሰጧት ምላሽም ቢሆን እንዳችም አሳማኝነት የሌለው ጭፍን ውግዘት ሆኖ ነው ያኘሁት በግሌ፡፡ ‹‹… ከ97ቱ ምርጫ ወዲህ ፍርሃት የተጠናወተው ኢህአዴግ በተቃዋሚ ፓርቲዎች ውስጥ ሰላዮቹን አስርጎብናል (አሰማርቶብናል)›› ሲሉ አስረግጠው የተናገሩት የመኢአድ መሪ ለቀድሞው ‹‹ቅንጅት›› መፍረስ ብቻ ሳይሆን ዛሬም ድረስ ፓርቲያቸውን ለሚያምሰው የውስጥ ችግር ዋነኛ መንስኤው ‹‹የወያኔ ስውር እጅ›› እንደሆነ ጭምር ከመግለፃቸውም ባሻገር ዘንድሮ ምርጫ እንዳልተካሄደ ሊያሳምኑን ሞክረዋል፡፡

እነሱ ያቀረቡት ‹‹ቅድመ ሁኔታ›› ተሟልቶላቸው ካልተሳተፉ በስተቀር ለምርጫው ዕውቅና እንደማይሰጡ በተደጋጋሚ ስብሰባ መክረው ዘክረው መወሰናቸውን ከዘንድሮው የአካባቢ ምርጫ በፊት ከገለጹልን ፅንፈኛ ተቃዋሚዎች መካከል መኢአድ አንዱ እንደመሆኑ መጠን? ፕሬዚዳንቱ ኃይሉ ሻውል እውነታውን አምነው እንዲቀበሉ ባይጠበቅም የወቅቱን የፖለቲካ እንቅስቃሴ በተመለከተ ሲጠየቁ ‹‹የፖለቲካ እንቅስቃሴ አለ እንዴ?›› በሚል ምፀት ጋዜጠኛዋን መልሰው የመጠየቃቸው ጉዳይ ግን የሚያስገርም ነው፡፡ የሰውየውን ቃለ ምልልስ ከሁሉም በላይ እጅግ አሳፋሪ እንዲሆን ያደረገው ደግሞ ምን መሰላችሁ?‹‹ከአንዳንድ ክልሎች ስለሚፈናቀሉ ሰዎች ምን አስተያየት አለዎት?›› የሚል ጥያቄ ቀርቦላቸው ከአንድ የፖለቲካ ፓርቲ መሪ በማይጠበቅ የግዴለሽነት መንፈስ አደገኛ ምላሻቸውን የሰጡበት ንግግር (አነጋጋር) ነው፡፡

በተለይም ከደቡብ ሕዝቦች ክልል ተፈናቅለዋል በሚባሉ አማርኛ ተናጋሪ ወገኖቻችን ላይ ሆን ተብሎ የሚፈፀምባቸው አስተዳደራዊ በደል ያለ ለማስመሰል ሲሉ የተከበሩ የመኢአድ ፕሬዚዳንት ዘረኛ ፕሮፓጋንዳቸውን ያስተላለፉበትን ግግር እነሆ እንደወረደአ ቅርቤዋለሁና

አንባቢያን ተመልክታችሁ የየራሳችሁን ህሊናዊ ፍርድ ስጡበት፡፡ ‹‹በጣም አሰቃቂ ጉዳይ ነው፡፡›አሁን ለምሳሌ ደቡብ ክልል ቤንች ማጂ ዞን›አሁን ለምሳሌ ደቡብ ክልል ቤንች ማጂ ዞን ብትሔድ ብዙ አሰቃቂ ነገሮች አሉ፡፡ እኔ አሁን ጉዳዮን እንዲያጣሩልኝ ወደ ቦታው የላክሁዋቸው የአማራ ተወላጆች አይደሉም፡፡ ለምን ብትይ የአማራ ኬላ የሚባሉ አምስት ቦታዎች ስላሉ የአማራ ተወላጆች በዚያ እንዲያልፉ አይፈቀድላቸውም፡፡ ስለሆነም ነው ጉዳዩን እንዲያጣሩ የደቡብ ሰዎችን የላክሁት፡፡ አማራ ቢሔድማ መታወቂያው ታይቶ ይያዛል፡፡ አምስቱም ኬላዎች ላይ ፖሊስ ቆሞ እንደሚጠበቅ መረጃው የደረሰኝም በደቡብ ተወላጆች በኩል ነው…›› ብለዋል፡፡ የመኢአድ ፕሬዚዳንት፡፡

ኬላዎቹ ምን ምን እንደሚባሉ ወይም በየትኛው የቤንች ማጂ ዞን ወረዳዎች እንደሚገኙ ያብራሩላት ዘንድ ጋዜጠኛዋ መጠየቋ ባይቀርም፣ እርሳቸው ግን አሁንም ‹‹ለጊዜው ዝርዝሩን አምጡልኝ አላልኩም እንጂ እነዚህ ኬላዎች አሉ፡፡ በእያንዳንዱ ኬላም ጠባቂ ሚሊሻዎች ቆመዋል፡፡ አንዳንዱ አማራ ወደዚያው የቢዝነስ ስራ ኖሮት ለማለፍ ሲፈልግ እንኳን አንድ ሺህ ብር ጉቦ ክፈል እንደሚባልም ደርሰንበታል›› ከሚል የስማ በለው ወሬ ያለፈ ተጨባጭ ማስረጃ መጥቀስ አልቻሉም፡፡ ታዲያ ስለኚህ ሰው የፖለቲካ ስብዕና ትችት ለመፃፍ ስነሳ የሚዛናዊነት ጥያቄ ፈተና ቢሆንብኝ ምን ይገርማል? ዕውን ሰውየው ያውም እንደኛ አገር ባለው ውስብስብ ነባራዊ እውነታ ውስጥ አንድን የፖለቲካ ፓርቲ ለመምራት የሚያስችል ስብዕና አላቸውን?

ካለፈው ታሪካችን ጋር በተያያዘ ምክንያት የሚከሰቱ የዚህ ዓይነት ሀገራዊ ችግሮቻችንን በተለየ ጥንቃቄና የኃላፊነት ስሜት መያዝ እንደሚጠበቅብን እንኳንስ የመኢአድ ፕሬዚዳንትና እኔ ተራው ዜጋ የምንገነዘበው የጋራ ጉዳይ አይደለምን!? እርሳቸው ግን በክስተቱ ተፈናቅለዋል ለተባሉት ወገኖቻች ያሰቡ መስለው በሚቆሰቁሱት የዘረኝነት እሳት ችግሩን ለማባባስና ለርካሽ የፖለቲካ ትርፍ ማስገኛነት እንደ መልካም አጋጣሚ ሊጠቀሙበት ሲሞክሩ ነው የሚታዩት፡፡

እንደኔ እምነት ከላይ ለዋቢነት ያህል የቀረበው የኢንጂነር ሃይሉ ሻውል መርዘኛ ንግግር እርሳቸውም ሆኑ ፓርቲያቸው መኢአድ በመላው የሀገራችን ብሔሮች፣ብሔረሰቦችና ህዝቦች የዘመናት ትግል ተንኮታኩቶ ወደ ከርሰ መቃብር የወረደውን የግዛት አንድነት ዳግም ነፍስ እንዲዘራ ለማድረግ ሲሉ በተለይም ከክልሉ ውጭ የሚኖሩ የአማራ ተወላጆችን ከሌሎቹ ኢትዮጵያዊያን ወገኖቻቸው ጋር በመቻቻል መንፈስ እንዳይኖሩ የሚያደርግ ቅራኔ

እንዲፈጠር እንጂ፣ችግሩ ዘላቂ መፍትሔ እንዲሰጠው የማይፈልጉ መሆናቸውን መረዳት የሚቻል ይመስለኛል፡፡

ይህ ማለት ዳግም ኢንጂነሩና ጥቂት መሰሎቻቸው የሚናፍቁት በትረ ስልጣን ለመጨበጥ ሲሉ በአማራ ህዝብ ስም ከመነገድ እንደማይቦዝኑ የሚያረጋግጥ አስተዛዛቢ የፖለቲካ ቁማር እንደሆነ ግልፅ ነው፡፡ እንግዲያውስ እኔም እንደዚህ ዓይነቱን በእሳት እንደመጫወት የሚቆጠርና ኢትዮጵያውያንን ለጋራ ጥፋት ሊዳርግ የሚችል አገራዊ ችግር ለስልጣን መወጣጫነት ሊያውሉት የሚሞክሩ፣ህሊና ቢስ ፖለቲከኞችን በቸልታ መመልከት አይገባም፣የሚል እምነት ስላለኝ ነው ይህችን ትዝብት አዘል አስተያየት ለመፃፍ መውደዴ፡፡

ስለሆነም ለተከበሩ ‹‹የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት›› (መኢአድ) ፕሬዚዳንት ለኢንጂነር ኃይሉ ሻውል አሳፋሪ ንግግር ያለኝን ተቃውሞ ለመግለፅ ያህል ብቻ የሚከተሉትን ጥቂት አንቀፆች አስፍሬ ሃሳቤን አጠቃልላለሁ፡፡ እውነት እንነጋገር ከተባለ ኢህአዴግ በእርግጥም እርስዎ እንዳሉት ‹‹ፍርሃት የተጠናወተው ፓርቲ›› ቢሆን ኖሮ በዚህ መሰረተ ቢስ የስማ በለው ወሬ ዘረኝነትን ሲሰብኩበት እያየ እንዳላየ አያልፍም ነበርና እባክዎት ትዝብት እንኳን ይፍሩ፡፡ ደግሞስ እንዲህ እንደርስዎ ዓይነቶቹ ቅንጣት ታህል የሃላፊነት ስሜት ያልፈጠረባቸው ደንታ ቢስ ግለሰቦች የፖለቲካ ፓርቲ መሪዎች በሚኖሩባት የብዙ ህዝቦች ድህ አገር፣ስልጣን ላይ ያለው መንግስት አደጋ እንዳይፈጠ ቢፈራ ምን ያስገርማል? ለነገሩ የኢህአዴግ ጤናማ ጥንቃቄ በአቋራጭ መንገድ ስልጣን የመቀማት ህልማችሁን ለማሳካት አላመች ስላላችሁ ነው እንጂ እውነታውን ልቦናችሁ ሳያውቀው ቀርቶ አይደለም፡፡

ለማንኛውም ግን፣አንድ የፖለቲካ ፓርቲ መሪ የሆነ ሰው ሚዲያ ላይ ቀርቦ ያውም አንዳች ማስረጃ ሳይኖረው፣ ዘረኝነትን የሚያበረታታ ቀስቃሽ ንግግር ሲናገር መስማት ከማሳፈርም አልፎ ያስደነግጣል፡፡ ስለዚህም ለእርስዎና ለቢጤዎችዎ ሁሉ፣ የኢትዮጵያ አምላክ ልቦና ይስጣችሁ ነው የምለው፡፡